የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ሐዋላን ለማሳደግ የሚከተለውን ስትራቴጂ በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

(በኢብባ ገዥ አቶ ማሞ ምሕረቱ)

**የተከበራችሁ የባንክ ፕሬዚዳንቶችና የኢብባ የማነጅመንት አባላት**

**ክቡራትና ክቡራን**

1. ሁላችሁም እንደምታውቁት፣ ኢትዮጵያ ከቅርብ ወራት ወዲህ በተቀናጀና በተሟላ እንዲሁም የሀገሪቱን ገጽታና የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ አደረጃጀት ከመሠረቱ በሚለውጥ ታሪካዊ የለውጥ ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ሁለተኛውን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ የሪፎርም ሥራዎች፣ በተለይ በአብዛኞቹ ቁልፍ በሆኑ ማክሮ ተቋማት በኩል በመካሄድ ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም ፣ እንደ ማዕከላዊ ባንክነቱ፣ የተጣለበትን ሕዝባዊ፣ መንግሥታዊና ታሪካዊ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት በርካታ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከእነዚህም የሪፎርም ሥራዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ አዲስ የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፍ መዘርጋትና ሥራ ላይ ማዋል፣ እንዲሁም ለረጅም ዓመታት ሳይለወጥ የቆየውንና በርካታ ክፍተቶችና እጥረቶች የነበሩበትን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻልና የፋይናንስ ዘርፉን አካታችነት እንዲሁም ዕድገት የሚያሰፉ፣ የክፍያ ሥርዓቱንና የዲጂታል ፋይናንስ አጠቃቀሙን የሚደግፉ የፖሊሲ እርምጃዎችንና አሠራሮችን ማስተዋወቅና መተግበር ይገኙባቸዋል።

2. ሌሎች የሪፎርም ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ዛሬ ላነሣው የምፈልገው፣ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ከተደረገባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ የሆነውንና ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ጉልህ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለውን የውጭ ምንዛሪ ሐዋላ ለማሳደግ እስካሁን ስለተወሰዱት እርምጃዎችና ስለተገኘው ውጤት እንዲሁም በቀጣይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች እንዲሁም በባለድርሻ አካላት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ቅንጅታዊ አሠራር ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ይሆናል።

3. ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ከመግባቴ በፊት፣ ስለ ውጭ ምንዛሪ ሐዋላ ምንነትና ስለሚያስገኘው ጥቅም ለጋራ ግንዛቤ ያህል በመጠኑ ለማውሳት እፈልጋለሁ። በአጭሩ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ፣ የውጭ ምንዛሪ ሐዋላ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሀገር ቤት ለሚኖሩ ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው የውጭ ምንዛሪ በስጦታ ወይም በክፍያ መልክ የሚልኩበት አሠራር ነው። በመሆኑም፣ የውጭ ምንዛሪ ሐዋላ በአግባቡ ከተደራጀና በቅንጅት ከተመራ፣ ለግለሰቦችም ሆነ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ ለውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት፣ ለቁጠባና ኢንቨስትመንት እንዲሁም ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለድህነት ቅነሳ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

Sudan Street, Addis Ababa, Ethiopia
Tel: 6230 430 Fax: +251 115514 588
nbe.gov.et

ከሁሉ በላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈለገው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ልማት ላይ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ከኢትዮጵያ ቀጣይ ዕድገት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የልማት ጉዞ ባይተዋር ሳይሆን ባለቤት እንዲሆኑ ለማስቻል ነው።

4. የውጭ ምንዛሪ ሐዋላ ለሀገራችንም ሆነ ለሌሎች በርካታ አዳጊ ሀገራት ተጨባጭ እና እምቅ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ምንጭ ነው። ብዙዎቹ ሀገራት (ለምሳሌ ህንድ፣ ፊሊፒንስ፣ ሜክሲኮ እና ናይጄሪያ) ከዚህ ምንጭ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር የውጭ ምንዛሪ ያገኛሉ።

5. ለአብነት ያህል፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት በቢሊዮኖች የሚገመት የአሜሪካን ዶላር በግል ሐዋላ መልክ (በግለሰቦችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል) ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል። ከዚህ ውስጥ 76 በመቶ ያህሉ ከግለሰቦች የተላከ እንደሆነ ታወቋል። በመሆኑም፣ የግለሰቦች ሐዋላ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ ለግለሰቦች የኑሮ ዋስትና ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ፣ አመቺና አስቻይ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ጥቅሙ ከዚህ ይበልጥ ሊጨምር እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በተለይም፣ በውጭ ሀገራት ከሚኖሩ በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ብዛትና ከኢትዮጵያ የቆየ የመረዳዳት ባህል አኳያ ሲታይ፣ በሐዋላ ሊሰበሰብ የሚችል የውጭ ምንዛሪ ሀብት ሰፊና ለሀገርና ለሕዝብ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

6. እንዲህ ከሆነ ይህንን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዴት እናዳብረው?ምን ዓይነት የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ያስፈልጋሉ? የሚለው ጥያቄ ወሳኝ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማዳበር በተለይም የግለሰብ ሐዋላን ለማሳደግ የሚረዱ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ ጀምሯል። ቀደም ሲል ሀገሪቱ ስትመራበት የቆየው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት በሂደት ያስከትል የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት መቀዛቀዝ፣ የሕገ ወጥ የውጭ ምንዛሪ ገበያ መስፋፋትና የውጭ ምንዛሪ ሽሽት ለመግታት እንዲሁም ማክሮ ኢኮኖሚያዊ መዛባትን ለማስተካከልና ሀገሪቱ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ያላትንና ሊኖራት የሚገባውን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በማሰብ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደራችን ሥር ነቀል በሆነ መልኩ ከሐምሌ 22፣ 2016 ጀምሮ በገበያ ሥርዓት እንዲመራ አድርጓል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የተበታተኑና ውስብስብ የነበሩ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያዎች በአንድነት በማጠቃለል ወጥ፣ ቀላልና ተነባቢ ሰነድ እንዲሆን ተደርጓል።

7. መመሪያው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ አከፋፈትና አጠቃቀም ሁኔታዎችን፣ የሐዋላ አላላክ ዘዴዎችን፣ በገበያ የሚመራ የውጭ ምንዛሪ ግብይትን የሚያሳልጥና የፋይናንስ አካታችነትን የሚያጎለብት ነው። ለምሳሌ፣ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ለውጥ በተካሄደ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ በትይዩ ገበያና በባንኮች የውጭ ምንዛሪ ገበያ መካከል ያለው የተመን ልዩነት (ፕሪሚየም) በከፍተኛ ደረጃና በፍጥነት ቀንሷል። በሁለቱ ገበያዎች መካከል ከለውጡ በፊት 100 ፐርሰንት የነበረው የተመን ልዩነት፣ ከሐምሌ 22 እስከ ነሐሴ 29፣ 2016 ባሉ ቀናት ወደ 4 በመቶ ወርዷል። ይህም የትይዩ ገበያ አስፈላጊነትና ጥቅም ትርጉም እያጣና በአንጻራዊነትም እየተዳከመ መምጣቱን ያሳያል።

8. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያው በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና የውጭ ምንዛሪ ገበያው በጤናማ ውድድር ላይ የተመሠረተና ግልጽነትን የተላበሰ እንዲሆን ክትትልና ቁጥጥር በማድረጉ፣ እንዲሁም አዲስ የውጭ ምንዛሪ ጨረታ ሥርዓት በመጀመሩ በለውጡ የመጀመሪያ ቀናት በባንኮች ዘንድ በውጭ ምንዛሪ ግብይት ረገድ ይታይ የነበረው መደናገርና የተራራቀ የውጭ ምንዛሪ ተመን አወሳሰን እየተስተካከለና አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መልክ እየያዘ መጥቷል።

9. ከዚህ በተጨማሪ፣ በቅርብ ጊዜ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች እንዲቋቋሙ ፈቃድ ስለሚሰጥና ሁሉም ነገር የተመቻቸ በመሆኑ የሐዋላ ሥራ ለመሥራት የሚፈልጉ ሁሉ ፈቃድ እንዲያወጡና በዚህ መልካም ዕድል እንዲጠቀሙ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። በዚሁ ረገድ የብሔራዊ ባንክ መስፈርትን ለሚያሟሉ ድርጅቶች ህጋዊ ፍቃድ በመጭው ሳምንታት ውስጥ መሰጠት ይጀመራል። በይሁን እንጂ ይህ ሕጋዊ ዕድል ተመቻችቶ እያለ በሕገወጥ የሐዋላ ሥራ ላይ በተሰማሩት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ለማስገንዘብ እፈልጋለሁ።

10. የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው የወጪ ንግድ ገቢን ጨምሮ አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ገቢን በተለይም የውጭ ሐዋላን በእጅጉ እንደሚያሳድግ ይጠበቃል። በባንኮች የውጭ ምንዛሪ ተመንና በትይዩ ገበያ ተመን መካከል ያለው ተመን እየጠበበ መምጣቱ የሐዋላ ተቀባዮች ገቢ እንዲጨምር ያደርገዋል፤ የውጭ ሐዋላም በሕጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ቤት እንዲላክ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የውጭ ምንዛሪ ገቢ ያላቸው ዜጎችም ሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአካል ቀርበው ብቻ ሳይሆን ከሩቅም በዲጂታል ዘዴ የውጭ ምንዛሪ እንዲከፍቱና ሂሳባቸውን እንዲያንቀሳቅሱ፣ በሀገራቸው ጉዳይ የሩቅ ተመልካች ሳይሆኑ የሀገራቸው ዕድገትና ልማት ባለቤቶችና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ ነው።

11. በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያውን ይዞትና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ሁሉ ለማስተባበር ሰፊና ሁለገብ የዘመቻ ሥራ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭም ለማካሄድ ዝግጅቱን አጠናቋል። ባንኩ የተለያዩ ዲጂታልና መደበኛ የተግባቦት ስልቶችን በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ማግኛ ዘመቻውን በግንባር ቀደምነት ለመምራት ዝግጁ መሆኑን፣ ከዚህ በተጨማሪ፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱ በአጠቃላይ ለባንኮችና ለህብረተሰቡ የኢኮኖሚ ፍላጎት እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

12. ይህንንም ግብ ለማሳካት ባንኩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት፣ ማለትም በዋናነት ከባንኮች፣ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች ሁሉ ጋር በትብብር ለመሥራት ይፈልጋል። በተለይ ከሐዋላ እንቅስቃሴ ዋነኛ ተጠቃሚ የሚሆኑ ባንኮች፣ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች እንዲሁም ውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የዳያስፖራ አባላት ስለ አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ባንኮች ደንበኞቻቸው ያለውጣ ውረድ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚከፍቱበትንና የሚያንቀሳቅሱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የዳያስፖራው ማህበረሰብ በሀገር ውስጥ ለሚያካሂዱት ኢኮኖሚአዊ እንቅስቃሴ የብድር አገልግሎት የማመቻቸት፣ ለሚያደርጉት ተቀማጭ የውጭ ምንዛሪ ልዩና ማራኪ የወለድ አገልግሎት የመስጠት ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችም ከባንኮች ጋር በቅንጅትና በግልጸኝነት የመሥራትና ለሐዋላ አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ወጪ ተመጣጣኝ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

13. ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፣ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገር ቤት የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ በመክፈትም ሆነ ሐዋላን በሕጋዊ መንገድ በባንክ ሥርዓት በመላክ፣ በሀገራቸው ልማት የራሳቸውን አሻራ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል። በየሀገሩ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላ ጽ/ቤቶች ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችና ኢንቨስተሮች ስለ ውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያና ተዛማጅ ጉዳዮች ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ወይም እንዲሰጥ በማድረግ፣ መመሪያውንም በማስተዋወቅ ረገድ የበኩላቸውን ሚና እንደሚወጡ ይጠበቃል። የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና በዚህ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሌሎች ተቋማት ተቀጥረው ወደ ውጭ የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ከሀገር ከመውጣታቸው በፊት ስለ ፋይናንስ አገልግሎቶች እንዲያውቁ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ፣ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎች(fintech's) ለአጠቃቀም ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርቡ ጥሪ ቀርቦላቸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም በሚሊዮን ለሚቆጠሩ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጭ ምንዛሪ ሀብታቸውን ለሀገር ዕድገትና ብልጽግና ማዋል የሚያስችላቸውን ለአጠቃቀም ምቹና ደህንነታቸው አስተማማኝ የሆኑ ዲጂታል ዘዴዎችንና የባንክ ሶሉሽኖችን አዘጋጅቶ ለማቅረብ ዝግጅቱን ጨርሷል። ከዛሬ ጀምሮ ለቀጣይ 6 ወራት የሚቆይ ፕሮግራም እየተጀመረ ሲሆን፣ በውጭ ምንዛሪ ሐዋላ ለሚሳተፉ አካላት በሙሉ የሚጠቅሙ ከዚህ የሚከተሉ ተጨማሪ እርምጃዎችን ይፋ እናደርጋለን፡-

ሀ) ባንኮች ለውጭ ሐዋላ ላኪዎች አበረታች የሆነ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲሰጡ ይበረታታሉ፤

ለ) መመዘኛውን የሚያሟሉ ሐዋላ ተቀባዮች በሀገር ውስጥ፣ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፤

ሐ) ሁሉም ባንኮች በጋራ ከሐዋላ ጋር በተያያዘ ብር 100 ቢሊየን ብድር አዘጋጅተዋል። ይህም ብድር በውጭ የሚኖሩና በሀገር ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ለከፈቱና ለሚከፍቱ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለቤት መሥሪያና ለሌሎችም ኢንቨስትመንቶች ብድር የሚውል ይሆናል።

መ) በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በያሉበት ሆነው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፤ ላስቀመጡትና ለሚያስቀምጡት የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ላይ የተሻለ ወለድ ይከፈላቸዋል።

ሠ) የውጭ ምንዛሪ ሐዋላን ለመሳብ እንዲቻል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሐዋላ ላኪዎች ከፍተኛ ዋጋ ያለው፣ እጅግ ፈጣንና ከፍተኛ እምነት የሚጣልበት የርቀት (ኦንላይን) መተግበሪያ unite.et ዛሬ ይፋ ያደርጋል።

14. በመጨረሻም፣ ለማሳሰብ የምፈልገው ነገር ቢኖር፣ ይህን ሀገራዊ ፕሮግራም በማሳካት ረገድ በተለይ ከእናንተ ከባንክ ፕሬዚዳንቶች ብዙ የሚጠበቅ መሆኑን ነው። ባንኮች የብሔራዊ ባንክ አዲሱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያ በትጋትና በጥንቃቄ ከመፈጸምና ከማስፈጸም ባሻገር፣ የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ ከሕገ ወጥ አሠራር የጸዳ እንዲሆን፣ የውጭ ምንዛሪ ሐዋላ መቀበያ፣ ማስተላለፊያና መጠቀሚያ ስልቶችን ለአሠራር ምቹና ቀልጣፋ ማድረግ፣ በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ደንበኞቻቸውን በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል ይጠበቅባቸዋል። በዚህም እናንተ የምትመሯቸው ባንኮች፣ ደንበኞቻችሁና መላው ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አውቃችሁ ለብሔራዊ ባንክ ሁለገብ ዘመቻ ተባባሪ እንድትሆኑ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

አመሰግናለሁ!